ቅድስተ-ቅዱሳን ድንግል ማርያም

(በሮማ ካቶሊክ፥ በፕሮቴስታንትና በኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት የሚሰጣት ግንዛቤና አክብሮት)

መስከረም ፲፯ ቀን ፪ሺ ፪ ዓ/ም
ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ nigatuasteraye@yahoo.com

አምስቱ አኀት አብያተ ክርስቲያናትም ኾኑ መላው ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ለእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የሚሰጧት ግንዛቤና ክብር አንድ አይነት ነው። በዚህም እምነታችን ከሮማ ካቶሊክና ከመላ ፕሮቴስታንት ምዕራባውያን አብያተ ክርስቲያናት እንለያለን። በዚህ ጽሑፍ ሊቃውንት አበው ካስተማሩኝ ሳልወጣ መጽሐፍ ቅዱስን፥ ዓበይት የጥንት ሃይማኖት መጻሕፍትንና የሃይማኖት ምርምር ውጤቶችን በመዳሰስ ልዩነታችንን እና አንድነታችንን ለመግለጽ እሞክራለሁ።

የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን:- *"Augustine declares triumphatly that, although "we did not yet have individually created and apportioned forms in which to live as individuals," what did exist already was the "nature of the semen from which we were to be prpagated. That semen itself, Augustine argues, already Shackled by the bond of death." transmites the damage incurred by sin"(Elaine Pagle, Adam and serpent, page 109)*

እ.አ.አ በ354 ዓ.ም. ከወንድ ዘር ተወልዶ ወደዚህ ዓለም የሚመጣ ሁሉ ከሞት የማያመልጥ መሆኑን አውግስቲን የተባለው ጽፎ ነበር። ዳሩ ግን የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲን እመቤታችንን ከሌላው የሰው ዘር ለመለየት በImmaculate Conception ተጸንሳ ተወለደች ብላ እንደ እ.አ.አ. በ 1854 ዓ.ም. አወጀች። *(Dictionary of Philosophy and Religion)*

በሌላ በኩል ደግሞ ይህ የካቶሊክ ትምህርትና እምነት እመቤታችንን ከአዳም ልጅነት አውጥቶ ከሰውነት ውጭ ስለሚአደርጋትና መለኮት የተዋሐደውን የክርስቶስንም ፍጹም ሰውነት ስለሚነካ መላው ኦርቶዶክስ አወገዘው። እንዲያ ውም አንዳንድ የካቶሊክ ጸሐፊዎች *Immaculate Conception* ከመሐጽፍ ቅዱስ የሚጠቀስ መረጃ የሌለው መሆኑን ይመሰክራሉ።
(http://www.justforcatholics.org/immaculate.htm)

ፕሮቴስታንቶች:-**ደግሞ ጌታችንን እስክትወልደው ድረስ ድንግል ነበረች ይሁን እንጅ ሰው በመሆኗ ክርስቶስን ከወለደች በኋላ ወደ "ልማደ አንስት" ገብታለች ይላሉ። የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ከነገረ መለኮቱ ርቃ እመቤታችንን ከሰውነት እንዳወጣቻት፥ ፕሮቴስታንቶችም የመጽሐፍ ቅዱሱን ግንዛቤ በመቁረጥ ብፅዕትነቷንና ቅድስተ ቅዱሳንነቷን ገፈዋታል። የኦርቶዶክስ ሊቃውንት ቅዱስ ሉቃስ ከጻፈው ወንጌል ሳይወጡ ለዚህም የሚከተለውን መልሰዋል ሰጥተዋል።**

ከጸነሰችበት ደቂቃ ጀምሮ የአምላክ ማደሪያ ከመሆኗም ባሸገር አምላክን ጸንሳ ወልዳ አሳድጋ ሁሉን በቅርብ እየተገዘበች የመጣች ስለሆነ፥ ከወለደችውማ በኋላ እንዲአውም ከነበራት የድንግልናና የቅድስና ክብር ወደ በለጠ ክብና ልዕልና

በመሻገር "ብጽዕትና ቅድስተ-ቅዱሳን" ሆነች:: ማለት ከዚህ ዓለም ሐሳብና ምኞት በሥጋዋም በሕሊናዋም ፈጽማ ራቀች:: ስለዚህ በሥጋዋም በሕሊናዋም ዘላለማዊት ድንግል ናት::

፭ኛ "ወማርያምሰ ተዐቅብ ዘንተ ኩሎ ነገረ ወትመይዮ ውስተ ልባ" (ሉቃ ፪:፲፰) ማለትም ከብሥራቱ ጀምሮ የሚካሄደውን ሁሉ መለኮታዊ ምሥጢር በመገንዘብ ሕሊናዋ የቃሉ መዝገብ ነበር:: ስለዚህ ሕሊናዋ ለዚህ ዓለም ኑሮና ጣጣ ድንግል ነበር::

፮ኛ "ወእሙሰ ተዐቅብ ዘንተ ኩሎ ነገረ ውስተ ልባ(ሉቃ ፪:፶፩) ማለትም የሚከናወኑትን ሁሉ የአምላክን ጥበብ እየተገረመች ሕሊናዋ በዚህ ዓለም ውስጥ አልነበረም::

፫ኛ"ወለኪሰ ይበውእ ውስተ ነፍስኪ ኩናት ከመ ይክስት ሕሊና ልቦሙ ለብዙሓን"(ሉቃ ፪:፴፭) የብዙዎቹን ሕሊናና አዕምሮ ለመቀየር የመጣው የማዳኑ ምሥጢርና ጥበብ የእርሷንም ነፍስ፥ ሥጋና ሕሊና እንደጦር ይወጋው እንደመንሽ ይበረብረው ስለበረ ስለዓለማዊ ነገር ለማሰብ ቅጽበት አልነበራትም:: ስለዚህ በሥጋዋም ድንግል በሕሊናዋም ድንግል ነበረች:: "እስከ አመ ወለደት ወልዳ ዘበኩራ" (የበኩር ልጇን እስክት ወልድ ድረስ) ለሚለው ሐረግ "እስከ እና ድረስ " የተባሉትን አገባቦች በመሸከሙ ለብዙወቹ እንቅፋት ስለሆነባቸው፥ በየጊዜው የጻፉ ሰዎች በብዙ ምሳሌና ማስረጃ ደጋግመው ስለገለጹት አልፈዋለሁ::

ኦርቶዶክሶች:- በኦርቶዶክሱ የነገረ መለኮት ትንተና ዘይቤ አንድ ነገር በቅዱሳት መጻሕፍት ተደጋግሞ ካልተነገረ በዶግማ ወይም በነገረ መለኮት ዘርፍ ውስጥ አይካተትም:: ለዚህም መረጃዎች:-

ሙሴ "በሦስት ምስክሮች ነገሮች ይጸናሉ"(ዘዳ ፲፱:፲፭) ብሎ እንደተናገረው::

ጌታችን ክርስቶስም "አንድ ወይም ሁለት ምስክር ካአንተ ጋር ውሰድ" (ማቴ ፲፰:፲፮) ብሎ እንዳጸደቀው፥

ቅዱስ ጳውሎስም "መንፈሳዊውን ነገር ከመንፈሳዊ ነገር በማስተያየት መንፈስ በሚያስተምረን ቃል እንናገራለን" (፩ኛ ቆሮ ፪:፲፩-፲፮) እንዳለው::

እነ ዲዮናስዮስም ከሐዋርያት ቀጥለው የተነሡት ሊቃውንት "ወዘንተ ትምህርተ ኀቡዓ ተምህርነ እምአምላክውያን ወኪያሁ ጸገውነ ወዝንቱ ትምህርት ኀቡዕ ለርኩሳን ወክሱት ለንጹሐን ጻድቃን የአምርዎ፡ ወኃጥአን ይስዕንዎ"(ሃ.አ. ምዕ ፲ ቁ ፲፯)) የምንከተለው የሃይማኖታችን ትምህርት ከእኛ በፊት ከነበሩት የአምላክ አገልጋዮች ከሆኑት የተቀበልነው ነው:: ንጹሕ መንፈስ ብሩህ አዕምሮ ያላቸው ያውቁታል:: በጥርጥር የተበከለ መንፈስ ላላቸው ለመቀበል ያቅታቸዋል፥ እንዳሉት፥ የኦርቶዶክስ ነገረ መለኮት ዶግማ በኦሪት በነብያት በሐዋርያት ተደጋግመው ባልተነገሩ ነገሮች ላይ አይመሠረትም::

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከአባቷ ከኢያቄምና ከእናቷ ከሐና በሩካቤ ሥጋ ያለ"Immaculate Conception" ተወለደች:: ጌታችንን ከመጽነሷ በፊት ድንግል፥ ንጽህት፥ ቅድስት ነበረች:: ጌታችንን ከጸነሰችበት ደቂቃ ጀምሮ ደግሞ ከኪሩቤል በላይ በመሆን ወደ "ቅድስተ-ቅዱሳንነት" ተሻገረች:: ፊላታዎስ የተባለው ሊቅ "እስመ በጊዜ ዘወረደ ላዕለ ድንግል ጎደረ ላዕሌሃ ጎይል አርያማዊ ከመ ያቅም እምኔሃ ብዕሴ ሐዲሰ" (ሃይማኖተ አበው ምዕ ፶፩: ቁጥር ፪) አለ:: ማለትም መንፈስ ቅዱስ በእርሷ ላይ ባደረ ጊዜ ሰማያዊ ኃይል ልጇ በማሕጸኗ አደረ:: ስለዚህ ኦርቶዶክሶች እርሷን ኃይል አርያማዊት ናትም አንልም:: የሚል ካለ የተወገዘ ይሁን እንላለን:: "እመቦ ዘይብል ከመ ድንግል ቅድስት ይእቲ ኃይል

አርያማዊት ውጉዘ ለይኩን" (ሃ.አ. ምዕ ፻፳፫:፻) እንደማነኛውም ሰው በዘር በሩካቤ ያለ"Immaculate conception" በመወለዷም ኃይል አርያማዊት አይደለችምና እንደሰው ሞተች:: "እስመ ነሥአ ሥጋ መዋቴ እስመ ቅድስት ድንግል ማርያም እንተ ነሥአ እምኔሃ መዋቲት ይእቲ"(ሃ. አ. ምዕ ፳፯ ቁ ፲፩)::ይሁን እንጅ እንደማነኛውም ሰው ትንሣኤ ዘጉባዔን ሳትጠብቅ በክብር ይህን ዓለም ለቃለች::

ስለ ጌታችን ሰው ሆኖ መወለድ ነብያት በገለጹት ትንቢታቸው ደጋግመው እመቤታችንን ቢያወሷትም ስለ እመቤታችን የሚሰጠው ትምህርትና የሚታመነው እምነት በሦስት ምስክሮች ከተረጋገጠው አይወርድም አይወጣም:: እነዚህም ምስክሮች መላኩ ቅዱስ ገብርኤል፥ ቅድስት ኤልሳቤጥና እራሷ እመቤታችን ናቸው::

፩ኛ የመጀመሪያው ምስክር መልአኩ **ቅዱስ ገብርኤል** ነው:: "ቃል ሥጋ"የሆነበትን ምሥጢር ሲያበሥራት የተናገረው ቃል፥ "ቃል ሥጋ" መሆኑን ብቻ አልነበረም:: የመጀመሪያ ንግግሩ ሰላምታና ማረጋጊያ ነበር:: ሁለተኛው ስለምትወልደው ልጇ ነበር::

ሀ:- የቅዱስ ገብርኤል የመጀመሪያው አቀራረብ "እጅግ የተባረክሽ ሆይ ደስ ይበልሽ፥ ሰላምታ ይገባሻል: እግዚአብሔር ካንቺ ጋር ነው:: አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ"(ሉቃ ፩:፳፰) የሚል ነበር:: በዚህ ጊዜ እመቤታችን ደነገጠች፥ ሰምታ የማታውቀው ድምጹና ንግግሩም እንግዳ ስለሆነባት አዕምሮዋ ጥያቄ ፈጠረ::

ለ:- የቅዱስ ገብርኤል ንግግር "በእግዚአብሔር ፊት ጸጋ አግኝተሻልና አትፍሪ: ትጸንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ::" (ሉቃ ፩:፴-፴፪) በማለት እያረጋጋ ብሥራቱን መንገር ነበር::

መ:-"ወንድ ስለማላውቅ እንዴት ይሆንልኛል?" ብላ ለጠየቀችው ቅዱስ ገብርኤል እንዴትና በምን ሁኔታ እንደሚከናወን እንዲህ ብሎ ገለጸላት:: "መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል:: የልዑል ኃይልም ይጋርድሻል:: የልዑል እግዚአብሔር ልጅም ይባላል" (ሉቃ፩፥፴፭) ብሎ መግለጽ ነበር:: ከዚህ በኋላ እመቤታችን ለጥያቄዋ የተሰጣትን መልስ በሙሉ ልቧ ተቀብላ "እንደ ቃልህ ይሁንልኝ" አለች:: በዚህች ደቂቃ ቃል ሥጋ ሆነ:: (ሉቃ ፩:፴፰-፴፭) ሦስት ረቂቅ ኃይላት፥ ከነ ስማቸውና ግብራቸው በመግለጽ ባንድ ፈቃድ፥ ባሕርይና አምላክነት በሰውነቷ እንደሚያከናውኑት ገለጸላት:: ይህ ምሥጢረ ሥላሴ የምንለው የክርስትና እምነትና ትምህርት መሠረት ነው::

ቅዱስ ገብርኤል ለሶስተኛ ጊዜ ጽንሰቱ እንዴት እንደሚከናወን የገለጸላት ንግግሩ፥ ምሥጢረ ሥላሴን፥ ምሥጢረ ሥጋዌንና፥ ምሥጢረ ጥምቀትን አካቶ የያዘ ነው:: የክርስትናን መሠረታዊ ሃይማኖት ያብራራ፥ የእርሷንም ማንነት የገለጸ ነው::
ይህን በቦታው ስንደርስ እንመለከተዋለን አሁን የሁለተኛዋን ምስክር የቅድስት ኤልሳቤጥን ቃል እንመለከታለን::

፪ኛ ምስክር ቅድስት ኤልሳቤጥ ናት::

"አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ የማኅጸንሽም ፍሬ የተባረከ ነው . . . ከጌታ የተነገረላትን ቃል ያመነች ብፅዕት ናት" (ሉቃ ፩:፵፩-፵፭) ብላ መሰከረች ቅድስት ኤልሳቤጥ ቅዱስ ገብርኤል ሲያበሥራት አልነበረችም:: መጽነሷንና እንዴት እንደጸነሰችም እመቤታችን አልነገረቻትም:: "መንፈስ ቅዱስ ሞላባት" ስለሚል ይህ የኤልሳቤጥ ቃል የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ቃል ነበር:: ብጽዕት የሚለው ቃል ለማንም ያልተሰጠ በቅዱስ ገብርኤልና በኤልሳቤጥ አንደበት በኋላም በራሷ በእመቤታችን አንደበት የተገለጸ ከሴቶች በመለየቷ እግዚአብሔር የሰጣት የልዕልናዋ ስም ነው::

፫ኛ ምስክር እራሷ እመቤታችን ናት::

"ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች:መንፈሴም በእምላኬና በመድኃኒቴ ሐሴት ታደርጋለችየባሪያውን ትሕትና ተመልክቷልና:: ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብጽዕት ይሉኛል:: ብርቱ የሆነ እርሱ በእኔ ታላቅ ሥራ አድርጓልና ስሙም የተቀደሰ ነው::"(ሉቃ ፩:፵፮-፶፩) ብላ መሰከረች:: "አሰስሎ ኃጢአት እግዚአብሔር ቃል በለቢሶተ ሥጋሃ ለእግዝእትነ ማርያም ሥጋ ዘነሥአ እምኔነ ወሞየ ለዘራዔ ኃጢአት በሥጋሁ ወወደዮ ውስተ ጻሕረ ደይን" (ሃይ. አበው ምዕ ፻፲፯:፭) የእመቤታችን ምስክርነትም በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ተረጋግጦ በመላኩ የደረሳት ስለሆነ የኦርቶዶክስ ነገረ መለኮት በዚህ መንገድ የተሰጣትን ክብሯንና ልዕልናዋን በድንግልናዋ በቅድስትነቷና በቅድስተ ቅዱሳንነቷ በሚድነቅ የሚገልጻትን ቅጽሎቿን ላብራራ::

ድንግልና:- ለአምላክ እናትነት የተዘጋጀችው እመቤታችን ይቅርና በሥርአት ያደገች ልጓገረድ የመጀመሪያ ልጇን እስክትወልድ ድረስ በድንግልና ተጠብቃ መቆየት በአገራችን እስከቅርብ ጊዜ ድረስ የተለመደና ይጠበቅ የነበረ ባህል ስለነበረ እመቤታችን ጌታችንን እስክትወልድ ድረስ ድንግልናዋ የተጠበቀ መሆኑ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን የሚአስገርምና የሚያጠራጥር አይሆንም:: የሚአስደንቀውና ከሴቶች ሁሉ የተለየች የሚአደርጋት ዘላለማዊ ድንግልናዋ ነው:: "አነሂ እብለከ ይእዜ ምንት ውእቱ ፅንስ ዘእንበለ ዘርእ ወወሊድ እንበለ መወልዲት ወኢእንበለ ሕማም ወእንበለ ይማስን ድንግልናሃ ድንግል ኮነት ወላዲተ ወነበረት እንዘ ሕቱም ማኅተመ ድንግልናሃ" (ሃይ አ: ምዕ ፻፱:፻፷)

ቅድስት:- የሚለው ቅጽልም ለእናቷ ለቅድስት ሐና፣ ለቅድስት ኤልሳቤጥና ለ፻፭ቱ ቅዱሳት ሴቶች ብቻ አይደለም:: ለአንዳንድ እጎቶቻችንም ሁሉ መጠሪያ ስም ሆኖ ስለተሰጠ እመቤታችን ቅድስት ብትባል አያስደንቅም:: የሚያስደንቀው ክርስቶስን በጸነሰችበት ቅጽበትና ከዚያም በኋላ የተሰጣት ብፅዕትና ቅድስተ ቅዱሳን ተብላ የምትጠራባቸው ቅጽሎቿ ናቸው::

ብፅዕት:- ይህ ቅጽል ከእግዚአብሔር የተላከው ቅዱስ ገብርኤልና፣ (ሉቃ ፩:፳፰) በምልአተ መንፈስ ቅዱስ ተሞልታ ቅድስት ኤልሳቤጥ የተናገረችው፣(ሉቃ ፩: ፵፪-፵፭) እንደገና በኋላም በራሷ ምስክርነት የተረጋገጠ ስለሆነ (ሉቃ ፩: ፵፰) ይህ አዋጅ እመቤታችንን ከሴቶች ሁሉ ለይቷታል:: አባቶች የሚጠነቀቁት ከዚህ ላይ

ነው:: አሁን የዘመኑ ሰባኪዎች "ከሰው ሁሉ የተለየች ናት" እያሉ እንደሚሰብኩት አላስተማሩንም:: ይህ ከኦርቶዶክስ ካረረ መለኮት ፈጽሞ የራቀ ነው:: የመጨረሻ ስሕተት ነው:: ቅዱስ ገብርኤልና ቅድስት ኤልሳቤጥ እንደተናገሩት እመቤታችን የተለየችው ከሴቶች ብቻ ነው:: ይህም በሴቶች ላይ የሚደርሰው ልማድ ነው:: ይህንንም "ልማደ አንስት" ብለው አባቶች ተርጉመውታል::

ቅድስተ-ቅዱሳን:- ያስተማሩኝ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት፥ ያራቱ የተዋሕዶ ኦርቶዶክሳውያንና የቀሩት ሁሉ ምሥራቃውያን ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያን ሊቃውንት ተስማምተው እመቤታችንን ከፍ አድርገው የሚገልጿት ከዚህ ጀምረው ነው:: እንዴትና መቼ ቅድስተ ቅዱሳን እንደሆነች ቅዱስ ኤፍሬም ከደረሰው ከውዳሴ ማርያሙ ጀምሮ ስለእርሷ የተጻፉት መጻሕፍት ሁሉ፥ ሰውን ሰው ከሚአደርገው ከሰባዊ አጽቅ ወይም ከወንድ ዘር በተለየ መንግድ እንደ ልጇ በግብረ መንፈስ ቅዱስ ወይም ያለ ጥንተ አብሶ በ(Immaculate Conception) ተወለድሽ የሚል የለም:: ልጇን ክርስቶስን ብቻ እንጅ እርሷን በዚህ መንገድ ተወልደሽ የመጣሽ ብሎ የተናገረ አንድም የኦርቶዶክስ አባት የለም::

ኦርቶድክሶች ጌታችንን ከመጽነሷ በፊት የነበራትን ድንግልናና ቅድስና ይዘው፥ ለሰጣት ምስጋናና ክብር የገለጹት ምክንያት ያለ (Immaculate conception) ስለተወለድሽ ብለው አይደለም::ጌታችንን ያለወንድ ዘር በ(Immaculate Conception)ከጸነሰችበት ደቂቃ ማደሪያው ስለሆንሽ እናቱ ስለሆንሽ፥ መቅደሱ ስለሆንሽ እያሉ ነው::

፬ኛ ቅድስት ድንግል ማርያም ያለ Immaculate Coneception ለመወለዷ ሌሎች ማስረጃዎች፥

1. ውዳሴ ማርያም

ከእጉድ:-"ተሰመይኪ ፍቅርተ ኦ ቡርክት እም አንስት"
ትርጉም:- (ከሴቶች የተለየሽ የተባረክሽው ሆይ እጅግ የተወደድሽ ተባልሽ)
ምክንያት:-"ቀዳሚት ቀመር ለኢየሱስ ክርስቶስ ዘተሰብአ እምኔኪ ዘእንበለ ውላጤ"
ትርጉም:- (ጌታችን ኢየሱስ ባሕርየ መለኮቱን ሳይለውጥ በማሕጸንሽ ስለተቀረጸ)

ሰኞ:- ተፈሥሒ ኦ ቤተልሔም ሀገሮሙ ለነብያት
ትርጉም:-ነብያት በመንፈስ ትንቢት የኖሩብሽ ቤተልሄም ሆይ ደስ ይበልሽ
ምክንያት:- እስመ ቦኔኪ ተወልደ ክርስቶስ
ትርጉም:- ክርስቶስ ካንች ተወልዷልና

ማክሰኞ:-ዕበያ ለድንግል ኢይትከሐል ለተነግሮ
ትርጉም:- የድግልን ክብር የሰው ቋንቋ ከሚገልጸው በላይ ነው
ምክንያት:-እስመ እግዚእ ሐረያ መፅአ ወሐደረ ላዕሌሃ
ትርጉም:-ጌታ መርጦ ማደሪያው አድርጓታልና

ረቡዕ:-የወቢ ክብራ ለማርያም እምኩሉሙ ቅዱሳን
ትርጉም:-የእመቤታችን ማርያም ክብር ከቅዱሳን ሁሉ ይበልጣል
ምክንያት:-እስመ ድልወ ኮነት ለተወክፎ ቃለ አብ
ትርጉም:- ቃል የተባለውን ጌታችንን ለመቀበል በቅታ ተገኝታለችና

ሐሙስ:-አዝ መንክር ወዕጹብ ኃይለ ከርሳ ለድንግል
ትርጉም:-በማኅጸኗ የተከናወነው ሥራ ምንኛ ያስደንቃል
ምክንያት:-ወላዲተ አእምላክ ዘእንበለ ዘር
ትርጉም:-ያለወንድ ዘር በአሁኑ አነጋገር ያለ ጥንተ አብሶ በ(Immaculate Conception) አምላክን ወልዳለችና::

ከዓርብ:-ቡርክት አንቲ ወተአብዩ እምሰማይ. . .ወሱራፌል ይሴብሑኪ
ትርጉም:- የተባረክሽ ከሴቶች ሁሉ ትበልጫለሽ፡ ሱራፌልም ያመሰግኑሻል
ምክንያት:-እስመ ዘይኅበር ዲበ ኪሩቤል ወሱራፌል መጽአ ወኀደረ ውስተ ከርስኪ
ትርጉም:- በዘባነ ኪሩብ ሆኖ የሚመለከው ጌታ በማሕጸንሽ አድሯልና

ከቀዳሚት:-"ተፈስሂ ኦ ምልእተ ጸጋ . ."
ትርጉም:- ፀጋን የተመላሽ ሆይ ደስ ይበልሽ
ምክንያት:- እስመ እምፍሬ ከርስኪ ኮነ መድኃኒተ ዘመድነ
ትርጉም:-ከማኅጸንሽ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተገኝቷልና

እስካሁን ድረስ ያየነው ቅዱስ ኤፍሬም እመቤታችንን ባወደሰበት አንቀጹ እንዲህ ስለሆንሽ እንዲያም ስለሆንሽ እያለ ከጌታችን ጽንሰት ጀምሮ ከጌታችን ጋራ በአላት ግንኙነት እያብራራ ተናግሯል:: በዚህ ኹሉ ሐተታው በእናትሽ ማሕጸን በ immaculate conception ተጸንሰሽ ስለተወለድሽ የሚል ባንድም ቦታ የለም:: የቅዱስ ኤፍሬም ውዳሴ ቅዱስ ገብርኤል ቅድስት ኤልሳቤጥና እራሷ "ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይለኛል፡ ምክንያቱም ብርቱ የሆነ እርሱ በእኔ ታላቅ ሥራ አርጓልና" (ሉቃ ፩፡፵፰-፵፱) ብላ ከተናገረችው ቃል ጋራ የሚስማማ ነው:: ገብርኤል ያልተናገረውን ኤልሳቤጥ ያላለችውን እራሷ ያልተናገራችውን ቃል ቅዱስ ኤፍሬም በድርሰቱ አላስገባም:: አሁን ደግሞ አንቀጸ ብርሃኑን እንመልከት::

2. አንቀጸ ብርሃን:-ሥላሴ ያከናወኑትን ይገልጻል

ሀ. "አብ በየማኑ ከደነኪ፡ (አብ በቀኙ ከለለሽ)
ወኃይለ ልዑል አጽንአኪ፡ (የልዑል ኃይል ጋረደሽ)
ወኢየሱስ ለብሰ ሥጋ ዚአኪ፡" (ኢየሱም ሥጋሽን ለበሰ:: ይህ ቃል እመቤታችንን እንደቃልህ ይኹንልኝ ያሰኛት ቃል ነው:: መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል "መንፈስ ቅዱስ በአንች ላይ ይመጣል:: የልዑል ኃይልም ይጸልልሻል:: ካለ በኋላ "ስለዚህ" ብሎ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል::" እያለ ስማቸውን ከነግብራቸው የገለጻቸው ያለ ታላቅ ቁምነገር በከንቱ የተናገራቸው አይደሉም:: ሥላሴ በተለየ ግብራቸው በማሕጸኗ ቃል ሥጋ እንዲሆን የተባበሩበት፡ በዚያው ቅጽበት የተቀደሰችበት ስለሆነ እመቤታችን በተጠቀሰችበት ቦታ ሁሉ "አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ" ሳይገለጹ አይታለፉም::

ለ. አንቲ ውእቱ ዘኮንኪ ጽርሐ ቅድሳት ወመቅደሰ ቅድሰተ ቅዱሳን . . .

ትርጉም:-የቅድስና አዳራሽ ከቅድሳት በላይም የቅድስና መቅደስ ሆንሽ
ምክንያት:- "በእንተ ቅዱስ መንፈስ ዘመጽአ ላእሌኪ ወኃይለ ልዑል ጸለለኪ ወመንጦላእተ ብርሃንሰ በእንተ ዘተሰወረ ቃለ አብ ኢየሱስ ክርስቶስ መድኃኒነ ውስተ ክርስኪ. . ."

ትርጉም:-መንፈስ ቅዱስ በላይሽ ስላደረ:: አብ ስለጠበቀሽ:: ጌታችን በማሕጸንሽ ሲያድር ሰውነትሽ ለብርሃን ልጅሽ መጋረጃ ስለሆንሽ እያለ ያደንቃታል:: ያለ ጥንተ አብሶ በ(Immaculate Conception) ተጸንሰሽ ስለተወለድሽ የሚል የለም:: አሁን ደግሞ በየደብሩና ገዳማቱ ያሉ ሊቃውንት ኦርቶዶክሳውያን በፍልሰታ እና በዘመነ ጽጌ የሚያነቡትን ስለክብሯ የሚናገረውን አርጋኖን የተባለውን መጽሐፍ እንመለከታለን::

3. መጽሐፈ አርጋኖን:-

ይህ መጽሐፍ የምሥጢረ ሥጋዌን ነገር በአንክሮ እየተመለከቱ በእመቤታችን ማሕጸን የጀመረውን የማዳኑን ጥበብ እያስታወሱ እመቤታችንን የሚያወድሱበት መጽሐፍ ነው:: ይህን መጽሐፍ የጠቀስኩት ስለ እመቤታችን ክብርና ውዳሴ ብቻ ስለሚገልጽ ነው:: በፍልሰታ ጾምና በዘመነ ጽጌ የጥንት ክርስቲያኖች የሚደግሙት መጽሐፍ ስለሆነም ነው::

መጽሐፉ እንደ ውዳሴ ማርያሙ፥ ቅዳሴ ማርያሙና ሌሎችም ኦርቶዶክሳውያን መጻሕፍት ከቅዱስ ገብርኤል፥ ከቅድስት ኤልሳቤጥና ከራሷ ከእመቤታችን አነጋገር አልወጣም:: እንደ ውዳሴ ማርያሙ ከእሁድ እስከ ቅዳሜ ባሉት ዕለታት የተከፈለ ነው:: መጽሐፉ እመቤታችንን ይቅርና ጌታችን የተኛበትን በረት የተጠቀለለበትን ጨርቅ ከእርሷ ጋራ አብሮ መወሳት ያለበትን ነገር ሁሉ ሳይቀር እየጠቀሰ ክብሯንና ልዕልናዋን ይገልጻል::"እትመሐጸን በጽላሎተ እግዚአብሔር ዘጸለለኪ ወአጽንአኪ ከመ ትኩኒ ታቦተ ወልዱ እትመሐጸን በትስብእተ ቃል እምኔኪ ዘእንበለ ተመያጥ፥ እትመሐጸን በልደተ ቃል እምኔኪ እንዘ ኢይትበተክ ማኅተመ ድንግልናኪ እትመሐጸን በኃል ዘአስከብኪዮ ወበ አጽርቅት ዘጠበለልኪዮ"(ፎ፻፪) ለመለኮት ማደሪያው ትሆኝ ዘንድ እግዚአብሔር አብ አጸናሽ ጋረደሽ፥ መንፈስ ቅዱስም ጋረደሽ ቀደሰሽም:: ማኅተመ ድንግልናሽ ሳይለወጥ የወለድሽውን ልጅሽን እማጸናለሁ:: "ሐቌ ኢያቄም አቡኪ ወማሕጸነ ሐና እምኪ እለ ፈረዩ ኪያኪ ፍሬ ቡርክተ" አንችን ያመነጨ የኢያቄም አብራክ አንችን ያፈራ የሐና ማሕጸን እያለ ያደንቃል:: ካቶሊኮች"በImmaculate conception" ተጸንሳ ተወለደች የሚለውን ሊደግፍ ቀርቶ "ልደትኒ ኀሩም እምድንግል ዘእንበለ ቃለ አብ" (ገጽ ፪፻፯፷) ማለትም በድንግልና ያለፉካቤ "immaculate conception" ተጸንሶ መወለድ ከአብ ቃል በቀር: ማንም ፍጡር አይወለድም በተፈጥሮ ክልክል ነው: ይላል:: ስለዚህ እመቤታችን የተፈጠረች ናት እንጅ ፈጣሪ አይደለችምና እንደ ልጇ በ"immaculate conception" ተጸንሳ አለመወለዷን አጠንክሮ ይገልጻል:: ቅድስተ ቅዱሳን ነሽ እያሉ ኦርቶዶክሳውያን የሚያደንቋት ጌታን ከልማደ አንስት ውጭ ጸንሳ በመውለዷ ነው::"ንጽሐ ድንግልናኪ ዘኢማሰነ በወሊድ እስመ ቅድስተ ቅዱሳን አንቲ "ሰዓታት) ከእናቷ ማሕጸን መንፈስ ቅዱስ የጠበቃት ሰው ሆና በመፈጠሯ፥ ሰው ሆኖ እንደተፈጠረ እንደማንኛውም ሰው በራሷ በግሏ ሕሊናን የሚያደፈርስ ሥጋን የሚአጎድፍ ስሕተት በደል እንዳትሰራ ነው እንጅ በተለየ መንገድ በ (Immaculate Conceptione ተጸንሳ እንድትወለድ አደረጋት ማለት አይደለም::"ጸራቅሊጦስ አቀባ እምከርሰ እማ ከመ ኢትጌኒ::" "ከመ ኢትጌኒ" የምትለዋ ሐረግ ከናቷ ማሕጸን ጀምሮ መንፈስ ቅዱስ ጠበቃት የሚለውን ንግግር ከሮማውያን ካቶሊኮች ግንዛቤ ለመለየት የተቀመጠች ቁልፍ ቃል ናት::

እሱ ሰው ሆኖ በማሕጸኗ ባደረ ጊዜ መጋረጃው ሆናለች:: "ሶበ ውእቱ ሥጋ ኮነ: እስመ ኮነት ዓጽፈ ለመለኮት::" የክርስቶስ ግን ያለ ወንድ ዘር (ያለ ጥንተ አብሶ) (without original sin) በማሕጸን በተጸነሰ ጊዜ ሥጋውን ከመለኮቱ ጋራ እንዲወሐድ አደረገው:: ይህ አባባል እስክንድርያዊ ዮሐንስ ከዚህ በታች ከተናገረው ጋራ ይስማማል:: "ዝንቱ ዘረሰዮ ይትወሐድ ምስሌሁ እስከ ለዝሉፉ እንዘ ርኁቅ እምኃጢአት ዘይደሉ እም አመ ፈጠሮ በውስተ ከርስ"(ሃይ. አበው ምዕ ፮:፴፰) የቃል ከአንች አወላለድ የአብን ቃል ከቅዱስ ገብርኤል በጆሮሽ በመስማት ነው:: ስለዚህ እንደ ንብ ተመሰልሽ:: ቃል በመሰማት ጸንስሽዋልና:: እንደ ንቡ ክንፍም የመንፈስ ኃይል ጋረደሽ:: "ወልደተ ቃልኒ እምኔኪ ከመዝ ኮነ:: . . . . .ቃለ አብ ደምጸ ውስተ እዝንኪ በአፈ ገብርኤል ወበእንተ ዝ ተመሰልኪ በእንቆራ :: እስመ በሰሚአ ቃል ጸነስኪ ወህይንተ አክናፈ ንሕብ አክናፈ መንፈስ ቅዱስ ጸለለኪ" (ገጽ ፪፻፷፫) በማለት በጽንሰቱ የተከናወውን ገለጸ::

የልዑል ማደሪያው ስለሆነች እመቤታችንን እናክብራት ከፍም እናድርጋት "ናብያ ወናልዕላ ለማርያም በእንተ ኩነታ ማኅደሩ ለልዑል::" የተኛበት በረትም የተከበረ ዙፋን ሆነ:: "ኅል ኮነ ህየንተ መንበር ወበአት፡ ኮነ ህየንተ ጽርሐ አርያም" (ገጽ ፲፰-፲፱) ጌታችን የተወለደበትን በረቱንና ከበረቱ ጋራ የነበሩትን ቁሳውያን ነገሮች ሁሉ ሲያነሣ እመቤታችንን ግን ከሰባዊ አወላለድ ውጭ በ(immaculate conception) ተጸንሰሽ ተወለድሽ የሚል ባንድም ቦታ የለም:: እነዚህ ከዚህ በላይ የገለጽኳቸው ውዳሴዎች በተጠቀሱበት ቦታ ሁሉ በማነኛውም የኦርቶዶክስ መጽሐፍ በ "immaculate conception" ተጸንሳ ተወለደች የሚል ባንድም ቦታ የለም::

4. መጽሐፈ ቀንዲል:-

ደጋግ ሰዎችን በአሰብክበት እኛንም አስበን ብሎ መጽሐፉን የዘጋው "በከመ ተዘከርኮሙ ለአብርሃም ወለ ሣራ ወወሀብኮሙ ይስሐቅሃ: እምድኅረ ልሕቁ ወበልዩ ወኮኑ አረጋዌ ወእቤርተ:: ወበከመ ተዘከርኮሙ ለኢያቄም ወሐና ወወሀብኮሙ ድኅረ ድካም: እግዝእትነ ድንግለ ንጽሕተ ኀርዩተ ማርምሃ እነተ እምኔሃ ተሠገወ" ብሎ ነው:: ይህም ማለት አብርሃምና ሣራ ካረጁ ካፈጁ በኋላ ይስሐቅን ለመስጠት እንዳሰብካቸው፡ ሲመኙ ኖረው ተስፋ ከቆረጡ በኋላ አስበህ ዓለምን ለማዳን የሚወለደውን ክርስቶስን ለመውለድ የተመረጠችውን እመቤታችንን ለሐናና ኢያቄም የሰጠህ፡ ይላል:: ይህ አባባል እመቤታችን ይስሐቅ ከተወለደበት መንገድ በተለየ መንገድ አለመወለዷን የሚያሳይ ነው::

5. ሊቃውንት:-

ሀ. ቴዎድጦስ:- "ወተክፈ ልደተ ከማየ በመንክር ግብር እንዘ ውእቱ እግዚአብሔር ቃል ወሰመያ ለእግዝእትነ ማርያም ድንግል ወላዲቶ ወጽአ እምከርሣ እንዘ ድንግል ወኢረኩሰት በምንትኒ እምዘፈጠራ::"(ሃይ አበው ምዕ ፶፫:፭፪) ይህን ሲል ከልማደ አንስት ፈጽማ የራቀች እንደሆነች ለማሳየት እንጅ ከተፈጥሮ አወላለድ ውጭ በImmaculate conception ተጸንሳ ተወለደች ማለት አይደለም::

ለ. ኤራቅሊስ:-"ኮነ ሥጋ አሐደ ምስሌሁ በአካል ዘእም እግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ ሥጋ አምላካዊ እምትዝምደ ዚአነ ወእንዘ ውእቱ እመንፈስ ቅዱስ ቦቱ ነስፍስተ ሥጋ ነባቢት"(ሃይ አበው ምዕ ፵፰:፭፩) ይህ የሚያሳየው ጌታችን ያለወንድ ዘር በመወለዱ ከእኛ ቢለይም፡ እንደእኛ ከወንድና

ከሴት ከተወለደችው ከእመቤታችን ሙሉ ሰውነትን እንደወሰደ ነው::

"ኢያእመረ ምሥጢረ ዘይትፈጸም በእግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም" የሴፍ እመቤታችን ያለወንድ ዘር መጽነሷን አላወቀም ነበርና ተጨነቀ" እያእመረ . . . ለእንተ እንበለ ርኩስ .... ከመ ይእቲ ኮነት ርኩስተ እስከ አመ . . . (ሃይ ምዕ ፶፰:፳፰-፴፬) " በዝየ ነትአ ዘያሜክር . . . (፶፱:፳) ኤራቅሊስ በዚህ ጽሑፉ ላይ የሚያሳየው የሴፍ ያለወንድ ዘር መጽነሷን ባለመረዳቱ መቸገሩንና እርሷ ለዚህ ግብር አለመፈጠሯን የሴፍ አለማወቁን ለማሳየት ይህን ተናገረ እንጅ እመቤታችን ከሰባዊ አወላለድ ውጭ መፈጠሯን ለመናገር የተናገረው አይደለም:: እየደጋገመ "ርኩስ" ስላለና ብዙወችንም ያሳሳተ ስለሆነ ቢብራራ የሚበጅ ይመስለኛል:: የወንድ ዘር ርኩስነቱ ለእመቤታችን ማነጻን ለጌታችን አጸናነስ ብቻ ነው:: እመቤታችን ለተወለደችበት ለኢያቄም ዘር፥ እሷ ለተጸነሰችበት ለቅድስት ሐና ማሕጸን አይደለም:: በጠቅላላ አነጋገር እርኩስ ማለት ያለቦታው የሚገኝ ወይም የሚውል ማለት ነው:: ለምሳሌ እግዚአብሔር የፈጠረውን ሁሉ ጥሩ ነው ብሎታል:: ይሁን እንጅ ፈረሶች አሕዮች፥ አሳማወች: አይጦች ሁሉ ለፈጠራቸውና ለተፈጠሩለት አላማ ቅዱሳን ናቸው:: ለኛ ምግብነት ግን የተፈቀዱ ባለመሆናቸው ለምግብነት ተስማሚ አይደሉምና ባለመሆናቸው ርኩሳን ተባሉ:: ማለትም ለሰው ምግብነት የማይስማሙ ማለት ነው:: ስለዚህ የኤራቅሊስ አነጋገር ይህ ነው::

አሁንም ኤራቅሊስ በሌላ ቦታ መቅደስ ሲላት ጸንሳ ስለወለደች ነው::
"ኦ መቅደስ ዘኮነ ባቲ እግዚአብሔር ካህነ ወኢፈለሰ እምሕላዌሁ አላ በሳህሉ ለበሰ ክህነተ በከመ ሚመቱ ለመልከ ጼዴቅ" (ሃይ.አበው ምዕ ፶፰: ፲፯) በመልከ ጼዴቅ ሥርአተ ክሕነት እግዚአብሔር ባሕርዩን ሳይለውጥ ካሕንም መስዋእትም ሆኖ የቀደሰበሽ ቅድስተ ቅዱሳን ነሽ አላት::

ሐ. Augustine የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን እመቤታችንን በImmaculate Conception (ያለ ጥንተ አብሶ) ተወለደች የሚለውን እምነት በ1854 እ.ኤ.አ. በአዋጅ ከመቀበሏ በፊት፥ ይህን ትምህርት ለመጀመሪያ ጊዜ አጉልቶ የሰበከው አውግስቲን ቢሆንም፥ ያለ ወንድ ዘር ካልተወለደው ከክርስቶስ በቀር፥ ከእናትና ከአባት ተወልዶ ሰው ሆኖ የመጣ ሁሉ በዚህ የተካተተ ነው ብሏል:: "Augustine intends to prove that every human being is in bondage not only from birth but indeed from the moment of conception . And since he takes Adam as a corporate personality, Augustine applies his account of Adam's experience, disrupted by the first sin, to every one of his offspring except, of course, to Christ, conceived, Augustine ingeniously argued, without semen" (*Adam, Eve, and the Serpent, Elaine Pagels page 109)* ማለትም ማነኛውም በወንድ ዘር የተወለደ ሁሉ ያለወንድ ዘር ከተወለደው ከጌታችን በቀር ሁሉም ያዳም ልጅ ከሆነ ጥንተ አብሶ አለበት ብሏል:: አውግስቲን በዚህ አቋሙ እመቤታችንን በተመለከተ ኦርቶዶክስ ነበር:: እስካሁን የጠቀስኳቸው ከኢትዮጵያ ውጭ የተወለዱ መላ ኦርቶዶክሶች በተለይም እኛን ጨምሮ የሚአገናኙንን ሊቃውንት ነበር:: እስከ ቅርብ ጊዜ የነበሩት የኛ አባቶችም የጥንቶችን በመከተል ይህንኑ አጠንክረው አስተምረው ጽፈው አልፈዋል::

መ. ታላቁና አንጋፋው ኢትዮጵያዊው የቤተ ክርስቲያናችን ሊቅ መላከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ "መድሎተ አሚን" በተባለው መጽሐፋቸው ከገጽ ፲፯-

፭፩ እንደገለጹት፥ በ፲፬ኛው ክፍለ ዘመን የነበሩት አባቶቻችን የተዋሕዶው እምነት በሮማ ካቶሊኮች እምነት ለመቀየጥ የሚሞክሩትን የገሰጹ እነ አባ ዝክሪ እነ አባ ጳውሊ የተናገሩትን በመጥቀስ "መንፈስ ቅዱስ ለአንጽሖ ማለትም ትስብእትን ከአዳም መርገም አንጽቶ ቀድሶ ለተዋሕዶተ መለኮት የበቃ አደረገው" ብለው እንደመሰከሩ ጽፈዋል:: ይህም በቅርቡ እስኪቀየር ድረስ በአብነቱ ጉባዔ አባቶች ሊቃውንት ያስተማሩንና የመላ ኦርቶዶክሳውያን እምነት ነበር::

ሠ. ብጹዕ አቡነ ጎርጎርዮስ በ፲፱፻፫፭ ዓ/ም (*የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ*) በሚል ርእስ ባሳተሙት መጽሐፋቸው ገጽ ፻፸፭ ላይ ስለ ኤፌሶን ጉባዔ በሚተርከው ክፍል፥ ፔላጊዮስ የተባለ ሰው ከተወገዘባቸው ስሕተቶቹ ውስጥ አንዱ፥ "አዳም ባይበድልም መሞት ነበረበት:: የአዳም በደል (ጥንተ አብሶ) የጎዳው ራሱን ብቻ ነው:: ወደ ዘሮቹ አልተላለፈም:: የሰው ዘር በራሱ ሥራ እንጅ በአዳም በደል "ጥንተ አብሶ" አልሞተም:: አይሞትም:: በክርስቶስ መነሣትም አይነሣም" በማለቱ ነው ብለዋል::

በ(*Philosophy and Religion, በተባለው መጽሐፍ ገጽ 561*) ላይ ተብራርቶ እንደተገለጸው ይህ የፔላጊዮስ አባባል ክርስቶስ ለአዳም ልጆች ኃጢአትና በደል ሲል ሞተ የሚለውን የክርስትናን መሠረተ ትምህርት የሚደመስስና፥ ክርስቶስ የሞተው እንደማነኛውም ሰው የሰውኑቴን ግዴት ለመወጣት አድርጎ በማቅረቡና እመቤታችንም በሞት ያለፈችው በራሷ በሠራችው በደል እንጂ፥ ከአዳም በወረሰችው ሰውነቷ አለመሆኑን ስለሚሰብክ ከኦርቶዶክሱ ነገረ መለኮት ጋራ ተጋጭቷልና በኦርቶዶክሶች መወገዙ ተገቢ ነው::

ረ. አለቃ አያሌው ታምሩ:-

፩ኛ በ፲፱፻፶፫ "የኢትዮጵያ እምነት በሦስቱ ሕግጋት" በሚል ርእስ በጻፉት መጽሐፋቸው በገጽ ፹፭ ላይ የጸጋ ሰጊድ በሚለው ንኡስ ርእስ ቁጥር ፭፩ ላይ "መንፈስ ቅዱስ ሥጋዋንና ነፍሷን አንጽቶና ቀድሶ የአምላክ እናት ለመሆን አበቃት" ከማለት በቀር በImmaculate Conception (ያለ ትንጠ አብሶ) ተጸንሳ ተወለደች አላሉም::

፪ኛ በ፲፱፻፷፱ "ወላዲተ አምላክ በኢትዮጵያ" በሚል ርእስ ባሳተሙት መጽሐፋቸው በገጽ፷፯-፷፰ በቁጥር ፲ ላይ "እግዚአብሔር በልኁ ዓለምን ሲዋጅና ሁሉ አዲስ እንዲሆን ሲፈቅድ መበሥር መልአክ ገብርኤል መንፈስ ቅዱስ ያድርብሻል፥ የልዑል ኃይልም ይጸልልሻል፥ ስለዚህ ካንች የሚወለደው ቅዱስ ነው፥ የልዑል እግዚአብሔር ልጅም ይባላል" አላት:: ብለው የብሥራቱን መልእክት ሲተረጉሙ እንዲህ ብለዋል:: "በዚህ ቃል የድንግል ሥጋዋም ነፍሷም በመንፈስ ቅዱስ ተቀደሰ አዲስ ሕይወት አገኘ:: ካሉም በኋላ በመቀጠል "የልዑል ኃይል ወንድ ከማወቅ ድንግልና ከማጣት ዘር ከመቀበል በጠቅላላ ከዓለም ጠባይና ግብር ጠበቃት ስለዚህ የመጀመሪያውን ቅድስና ከሰው ልጆች ሁሉ በፊት ለእግዚአብሔር እናት በመሆኗ ታደለች:: በዚህ መሠረት "ሰውነቴ በአምላኬ በመድኃኒቴ ደስ ይላታል" ብላ ለመናገር በቃች::" ብለዋል:: ይህም እራሳቸው የፈጠሩት ሳይሆን የኦርቶዶክስ ሊቃውንት እነ ዘሱኑይ እነ ቄርሎስ ሁሉ የተናገሩት ነው:: "በሊሐ ልሳን ወልቡና መምሕር ቄርሎስ እንተ ጸሐፍዋ እንዘ ይብሉ ዐቀባ ለድንግል ንጽሕት ማርያም እንዘ ኢያርኁ ማኅተመ ግንግልናሃ እምድኅረ ልደተ ሕጻን እምኔሃ. . . ወውእቱ ንጹሕ እምፀቱ ግብራት እለ ሥሩአት በዕንለ እመሕያው ወእሙራት ቦሙ ዘውእቶሙ ሩካቤ ወዘርዕ ወሰስሎተ ድንግልና ከመ አልቦ ዘይትማሰሎ ለልደቱ እምኩሉ እንለ እመሕያው" (ሃይ አበው ምዕ ፻፲: ቁጥ

፳፱) እያሉ ጽፈውታል:: አስተምረውታል::

በዘመናችን ያሉ የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ሊቃውንትም "None of the ancient Holy Fathers say that God in miraculous fashion purified the Virgin Mary while yet in the womb; and many indicate that the Virgin Mary, just as all men, endured a battle with sinfulness, but was victorious over temptation and was saved by Her Divine Son" *(By blessed Archbishop Johan Maximovtch, The Orthodox Veneration of the Mother of God page 39)* እያሉ በጽሑፍም በቃልም የመላ ኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ አጉልተውና አጠንክረው ሳይመሰክሩትና ሳይናገሩት አላለፉም::

የዘመናችን ፓትርያርክ አቡነ ጳውሎስም ለዲግሪያቸው ጥናታዊ የነበረ መለኮት ንጽጽር ፍልሰታ በሚል ርእስ በጻፉት Dissertion (Thesis) የቤታችን ሊቃውንትና መላው ኦርቶዶክሶች፥ አኃት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የሚሉትን ደግመው ደጋግመው በመጥቀስ አረጋግጠው ጽፈውታል:: "ድንግል እመቤታችን በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ልዩ የክብር ቦታ አላት:: አማልጅነቷም ታላቅ ቦታ አለው:: ይህም በየጊዜው በሚደረገው ጸሎት ይነገራል:: አምላካችን ይቅር እንዲለን ጸሎታችንን ታቀርብልናለች:: ለሰው ዘር ሁሉ ትማልዳለች:: ይሁን እንጅ ከጥንተ አብሶ ነጻ ሆና አልተወለደችም:: ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ ለየት ባለመንገድ በተለየ መልክ ክርስቶስን ከመጽነሷ ተዘጋጅታለች" ብለዋል::

"The Virgin Mary occupies a unique place in the Ethiopian Orthodox Church. Her intercession is continually sought, evidenced by the common prayer of supplication:" our Lady Mary the Mother of God, offer up our prayer that our sins may forgiven." She pleads for the human race. She is not "Immaculate" in the sense that She was born without sin, but in the sense that she was specially prepared by the Holy Ghost"(*Bishop Poulos Yohanis, Filiseta pag 147-148)*

እመቤታችን እንደሌሎቹ የአዳም ሴትና ወንዶች ዘሮቹ በአዳም ኃጢአት ምክንያት ሞተች:: አዳም በሰራው ኃጢአት ሞተ:: እመቤታችን ግን የአዳም ዘር በመሆኗ በአዳም ኃጢአት (ጥንተ አብሶ) ምክንያት ሞተች:: የጌታችን ሰውነት ከእመቤታችን የተገኘ ሲሆን ኃጢአትን ይደመስ ዘንድ ሞተ ብለዋል:: "Like all daughters and sons of Adam, the holy Virgin Mary died as a result of Adam's sin. "Mary, sprung from Adam, died on consequence of original sin: Adam died in consequence of sin, and the flesh of the Lord, sprung from Mary, died to destroy sin."*(page 302)*

የሮማ ካቶሊክ ማእከላዊ እምነት አምልኮትና ትምህርት ማርያም በናቷ ማህጸን ስትጸነስ ጀምሮ ከጥንተ አብሶ ነጻ ናት:: ይህንንም immaculate coneception ብላ ሰይመዋለች::"central to Roman Catholic Marian devotion and teaching is the belief that the virgin Mary, from the first instant of her conception, was immune from the stain of original sin a privilege the Roman Catholic Church refers to as "immaculate conception."*(page v)* ብለዋል:: ቀጥለውም እንዲህ ብለው ነበር:: "ኢትዮጵያውያን ምእመናን ቅድስት ድንግ

ማርያም የአምላክ እናትን እኅታቸውም እንደሆነች ባይረሱም ሆኖም እሷም እንደነሱ የአዳም ዘርና የአብርሃምና የዳዊት ልጅ በመሆኗ እራሷ እንደኛ መዳን እንደሚያስፈልጋት ጠንቅቀው ያውቃሉ:: "The Ethiopian faithful never forget that the Virgin Mother of God is also their sister, the daughter of Adam, the descendant of Abraham and David, herself in need of redemption and therefore of salvation. 'Luk 1:46-47' ብለዋል:: *(Filiseta Page 40)*

እመቤታችንን እኅታችን ማለት የኢትዮጵያውያን አባባል ብቻ አይደለም:: ኦርቶዶክሶች ሁሉ የሚሉት ነው:: ለምሳሌ ቅዱስ አትናቴዎስ "ወኩሎሙ ሰብእ ረከቡ መድኀኒተ በሥጋሁ ለእግዚእነ ወመድኀኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ እስመ ሥጋሁ ውእቱ ምስለ ሥጋ ዚአነ:: ወእግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም እኅትነ ይእቲ እስመ ኩልነ እምነ አዳም ንሕነ" ብሏል:: (ሃይ አበው ምዕ ፶:፶፭) ቀጥተኛ እምነትና ትምህርት ሆኖ በመላ ኦርቶዶክሶች የነገረ መለኮት ሚዛን ተጠብቆ የኖረና መኖርም ያለበት ስለሆነ ለእኛ ብቻ የተሰጠ ልዩ ነገር አይደለም:: ከአኀት አብያተ ክርስቲያናት የተለየ የኦርቶዶክስ ነገረ መለኮት ትምህርትና እምነት የለንምና::

በዚሁ መጽሐፋቸው በ (ገጽ vii) ላይ ደግሞ፥ "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ነገረ መለኮት ብፅዕት ድንግል ማርያምን የእግዚአብሔር እናት አድርጎ፥ ሲመለከት በሌላ በኩል ደግሞ ሰው በመሆኗ በጥንተ አብሶ ጥላ ሥር ተወልዳለች:: " Ethiopian Orthodox theology sees the blessed Virgin Mary, Mother of God , on the one hand as honored by God above all other creatures in being chosen as the mother of God, the word incarnate, but on the other hand as a human being , born under the shadow of original sin, whose death and assumption into heaven represent the epitome of God's work of salvation for all of humanity in the most exalted member." እያሉ በመጽሐፋቸው መስክረውታል::

ከላይ የጠቀስኳቸውን የመሳሰሉ መረጃወች መሠረት በማድረግ የመላ ኦርቶድስም ሆነ ያገራችን ተዋሕድ እምነት ሊቃውንት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "እኛ ካስተማርናችሁ እምነት ውጭ ሌላ ከሰማይ እንኳ መጣሁ የሚል መላክ የሚቃረን ቢነግራችሁ የተወገዘ ይሁን:: "አንትሙሰ መልአክ እምሰማይ ለእመ መሐረክሙ ካልአ እምዘ መሐርናክሙ ውጉዘ ለይኩን:: በከመ እቤ ቀዳሚ ወይእዜኒ እብል ካዕበ ለእመቦ ዘመሐረክሙ ካልአ እምዘ መሀርናክሙ ውጉዘ ለይኩን::" (ገላ ፩:፰-፱) የሚለውን ሲጠብቁ ኖረዋል::

ለምሳሌ "ጸጋ የተመላው ቅዱስ ባስልዮስ፥ ለቀናው ሃይማኖት ድልድይና ምሰሶ የውቀት ሰው የሆነው አትናቴወስ፥ ጎርጎርዮስ፥ ዮሐንስ አፈወርቅና ጥበብ የተሞላው ቄርሎስ በነዚህ ሁሉ አንደበት የተሰበከው፥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረው በሐዋርያት የተሰበከው ነው:: ስለዚህ ከነሱ ትምህትና ምክር እንዳንናወጽ እንጠንቀቅ" ብለዋል:: "ወንትአመን በከመ ትምህርተ አበው ሐዋርያት ርቱዕነ ሃይማኖት ወአጽድቆቶሙ ዘንተ ሥርአተ ሃይማኖት ዘነበበ መንፈስ ቅዱስ በልሳናቲሆሙ ወፈድፋደሰ ንኩን እጉዛነ ወጽኑአነ በትምህርተ ባስልዮስ ዐቢይ አፈ በረከት ወአትናቴወስ ብእሲ ሐዋርያዊ መነፈደ ሃይማኖት ወመዝገበ ልቡና ወጎርጎርዮስ ዘኑሲስ ወዮሐንስ አፈወርቅ: ወቄርሎስ ጠቢብ እሉ እለ መርሑ ወአጽደቁ ወአርትዑ ሃይማኖተ እንተ ይእቲ በእግዚእነ ክርስቶስ::"(ሃይ. ምዕ. ፻፫: ቁጥ ፯)

መጽሐፈ ቅዳሴአችንም "ከኛ በፊት የነበሩትን በኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖት

ጸንተው ያለፉትን አበው እንምሰላቸው:: እንከተላቸውም" ካለ በኋላ "አምላካችን ሆይ
በማነኛውም ጊዜ በግብራችን በጠባያችን በእምነታችን እነሱን እንድንመስል ባለፉበት መከራና ሥቃይ ሁሉ ያለፉበት ፈተና ቢገጥመንም በፍቅርና በእምነት ተሳስረን እንደነሱ በኦርቶዶክሳዊት አምልኮ እንድንጸና በጸጋህ ደግፈን" "ንሑር በፍናዊሆሙ ወንትሉ በአሰሮሙ ወጸግወነ በኩሉ ጊዜ ንትመሰል ኪያሆሙ ወንጽንአ በፍቅሮሙ:: ወንኩን ክፍለ ምስሌሆሙ በውስተ ጻሚሆሙ በሠናይ አምልኮ::" (ሥ.አ.ቅ.ገጽ ፱፷ ቁጥ ፻፵፭) የሚለውን በሕይወታቸው እየተረጎሙት አልፈዋል:: የሚገርመው ነገር እኛም በተልምዶ ቅዳሴ በገባን ቁጥር እንለዋለን::

የመጀመሪያው ፓትርያርካችን ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስም በዘመናቸው ከነበሩት አበው ሊቃውንት ጋር ሆነው ሃይማኖተ አበው የተባለውን መጽሐፍ ካሳተሙ በኋላ "ሃይማኖተ አበው ማለት ከአባቶች ተያይዞ ለልጆች የደረሰ ወደፊትም የሚተላለፍ የማይለወጥ ማለት ነው እንጅ አባቶች ሲያልፉ አብሮ የሚአልፍ አይደለም" ብለው የተናገሩት ያደራ ቃል በ፲፱፻፹፮ ዓ/ም ድጋሚ በታተመው ሃይማኖተ አበው በሚባለው መጽሐፍ በመጨረሻው ገጽ ተጽፏል:: እስከነ ብፁዕ
አቡነ ጎርጎርዮስ ዘመን ድረስ የነበሩት ሁሉ ሊቃውንት አበው በቃላቸው በጽሑፋቸው ከጠበቀ አደራ ጋር ያቀበሉንን የአኀቲ ቤተ ክርስቲያንን እምነትና ትምህርት እንዳንጠብቅ ያፈዘዘንና ያደነግዘዘን አዚም ማን አዞረብን? ሊቃውንቱን ሁሉ ምን
በልቶ ጨረሳቸው?

በበኩሌ ባለኝ ኃላፊነት አምስቱ አኀት አብያተ ክርስቲያናትም ኾኑ መላው ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ለእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የሚሰጧት ግንዛቤና ክብር አንድ አይነት መሆኑን፡ በዚህም እምነታችንም ከሮማ ካቶሊክና ከመላ ፕሮቴስታንት ምዕራባውያን አብያተ ክርስቲያናት የምንለይ መሆናችን፡ ሊቃውንት አበው ካስተማሩኝ ሳልወጣ መጽሐፍ ቅዱስን፡ ዓበይት የጥንት ሃይማኖት መጻሕፍትንና የሃይማኖት ምርምር ውጤቶችን በዚህ ጽሑፍ በመዳሰስ ገልጫለሁ::

በተረፈ እመቤታችንን እጅግ ያከበራችሁና የቀደሳችሁ መስሏችሁ በስሕተት የገባውን የሮማ ካቶሊክን ትምህርትና እምነት ስታሰራጩ ከነበራችሁት ውስጥ እመቤታችን በImmaculate Conception" ካልተወለደች ለምን አባ ሕርያቆስ "ወሶበ ርእየ ንጽሕናኪ" አሉ? ተአምረ ማርያምስ ለምን "ነበረት በሕሊና አምላክ" አለ:: ቅዱስ ያሬድስ "ማርያምስ ተሐቱ እምትካት ውስተ ከርሱ ለአዳም ከመ ባሕርይ ፀዳ" ለምን አለ? የሚል ጥያቄ ስላላችሁ ከኦርቶዶክሱ ያተረጓጎም ይዘት ሳልወጣ ከዚህ ቀጥየ ገልጬ አቀርባለሁ::

ይቆየን

ማሳሰቢያ፡-

ምእመናን ሆይ!

የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ትምህርትን ሳይገ፟ዘቡ እየጸጸሱ እየቆመሱና እየቀሰሱ ወደ ቤተ ክርስቲያናችን በመግባት፥ በመዝሙራቸው በጽሑፋቸውና በስብከታቸው ሲአሰራጩ የ፟በሩ ሁሉ በሰሩት ስሕተት ተጸጽተው ከመመለስ ይልቅ፥ "አላዋቂ እንባላለን" በሚል ደካማ አስተሳሰባቸው በዚሁ በተሳሳተ እም፟ነታቸው ለመቀጠልና በሕዝቡ ስሜት እራሳቸውን ለመሰወር በመሞከር ሕዝቡ እንዲሸፍናቸው የሚጥሩ ሰወች ይኖራሉ:: በመጀመያ ባልደከሙበት ባልተማሩት ሙያ መግባትና ደፍሮ በማምት ያልሆ፟ ፟ነገረ መጻፍና ማሰራጨት ወንጀል ፟ው:: ኃጢአትም ፟ው:: ስለዚህ ማን አስተማራችሁ ብላችሁ ጠይቋቸው:: ኢትዮጵያን ለቅቄ እስክወጣ ድረስ "ከልጅልጅህ ተወልዴ አድንሐለሁ" በማለት ከአዳም ልጅ ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ተወልዶ አዳ፟ን" እየተባለ እንጅ የተወዘውን የሮማ ካቶሊኮችን ትምህርት "ጥንተ አብሶ" የሚል የግእዝ ቃል አልብሶ ለእመቤታችን የቅድስናዋ መግለጫ ሆኖ ተሰትጦ አያውቅም:: ይህ ጉዳይ የመጨረሻ ፟ውር፥ አሳፋሪና የተዋሕዶውን ፟ነገረ መለኮት የሚያናጋ ስለሆ፟ ባጠገባችሁ ያሉትን ካህናት "ከየት ተማራችሁት?" እያላችሁ አፋጣችሁ ያዟቸው::

ለሌሎች የቂሲስ አስተራየ ጽጌ ጦማሮች የሚከተለውን ድህረ-ገጽ ይመልከቱ፥

http://www.medhanialemeotcks.org/